# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ጳጉሜን 5 ቀን 2003 ዓ.ም**

## የአመቱ ማጠቃለያ

## ክፍል ሁለት

ባሳለፍነው ዓመት እስራት...... ስደት..... ርሀብ.....መፈናቀል.....መባረር ከደረሰባቸው የሀገሪቱ ዜጎች መሀከል የኢትዮጵያ ቲሌኮሙኒኬሽን ሰራተኞች ዋነኛና ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ቲሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የአሁኑ ኢትዮ-ቲሌኮም ሰራተኞች በሁለት ዙር የምንጠራ ዘመቻ ተደርጎባቸው ከ11 ሺ.ህ በላይ የተባረሩት እና ቤተሰቦቻቸውን በትነው ለጎዳና ህይወት የተዳረጉትም በዚሁ ዓመት ነበር፡፡

ቀድሞ ከነበሩት 13 ሺ.ህ ሰራተኞች መሀከል 8ሺ.ህ ያህሉን በመጀመሪያ ዙር ቀጥሎም 3 ሺ.ህ ያህሉን በሁለተኛው ዙር በአጠቃላይ 11 ሺ.ህ ያባረረው አዲሱ የወያኔ ቲሌ ኮም ድርጅት በስራ ላይ ተመድበው ከነበሩት 2 ሺ.ህ መሀከልም በድጋሚ የመባረር ዘመቻ ተወስዶባቸዋል፡፡

እውቀት ሳይሆን ለወያኔ ማጎብደድ...... ችሎታ ሳይሆን ወያኔ መሆን ዋነኛ መመዘኛ የሆነው የወያኔ የስራ ቅጥር መስፈርት ነባርና ልምድ ያላቸውን በተለይ የተማሩ ዜጎችን በሰበብ አስባብ እየመነጠረ በማባረሩ ሀገሪቱ ከግዜ ወደ ግዜ ወደ ውድቀት እንድታመራ ሆን ብሎ እየሰራ የነበረበት ዘመን እንደነበር በስፋት ዘግበናል፡፡

****

በምስራቅ ኢትዮጵያ ክልል ውስጥ በርሀብ እየሞቱ ያሉትን ዜጎች ለመታደግ እየተንቀሳቀሱ በነበሩት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የምግብ ፕሮግራም ሰራተኞች ላይ በተሰነዘረ ጥቃት አንድ ሲገደል ሌላ አንድ ክፉኛ በመቁሰሉ እንዲሁም ሁለት ሰራተኞቹ ታፍነው በመወሰዳቸው ድርጅቱ ስራውን አቁሞ ከአካባቢው ለቅቆ ወጥቶዋል፡፡

ከእንግዲህ ተቃዋሚ ታጣቂ ኃይል በሀገሪቱ ተወግዶዋል.....ፍጹም ተደምስሶዋል.....እያለ የወያኔ ቡድን የዓለምን ህዝብ ሲያታልል ከርሞ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የምግብ ፕሮግራም በድርቅ በተመታው የሱማሌ ክልል ውስጥ ሰራተኞቹን አሰማርቶ የሰብአዊ ተልዕኮውን እየተወጣ ባለበት ወቅት ድንገት ባልታወቁ ታጣቂዎች በነፍስ አድን ሰራተኞቹ ላይ በተወሰደባቸው ጥቃት ስራውን ለማቆም የተገደደውም በዚሁ ባሳለፍን ዓመት ነበር፡፡

****

ሰላም ሲሉት ጦርነት......እድገት ሲሉት ውድቀት......ዳቦ ሲሉት ድንጋይ የሚለው የወያኔ ቡድን በሀገሪቱ የኑሮ ውድነት ህዝቡን እግር ከወርች አስሮ ባለበት......በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በርሀብ እየረገፉ ባለበት አፍላ ግዜ የውስጥ ፖለቲካውን ለማርገብና የዓለም ሕበረተሰብን ለማጭበርበር ሲባል ያለ አንዳች ቅድመ ጥናት ድንገት በአባይ ወንዝ ላይ ግድብ መስራት በሚል አዲስ የቅስቀሳ ዘመቻ የጀመረው በዚሁ ዓመት አጋማሽ ላይ ነው፡፡

በአባይ ወንዝ ላይ ግድብ መስራት የሚለው የወያኔ ማሳሳቻ ፕሮፓጋንዳ የስልጣን እድሜ ለማራዘሚያነት እና ግዜ ለመግዣነት የታቀደ ባዶ ቅስቀሳ መሆኑን የሀገሪቱ ምሁራኖች እና ህዝቦች ትችትም ሲሰነዝሩበት ቆይተዋል፤ አሁንም የሰላ ትችት እየተሰነዘረበት ይገኛል፡፡

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በውስጥና በውጭ በተፈጠረበት የፖለቲካ ውጥረት ብሎም የአረብ ሀገራት የህዝባዊ አመጽ ወደ ሀገር ውስጥ ሊመጣ ይችላል በሚል ስጋት ሊያበርድልኝ ይችላል ሲል ሳይታሰብና ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ ከሱዳን ድንበር በ20 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ታላቁ የሚሊኒየም ግድብ ፕሮጄክት በሚል የመሰረት ድንጋይ መጣሉን ተከትሎ በምሁራኖች እና በባለሙያዎች ከፍተኛ ትችት እና ተቃውሞ እየቀረበበት ቢገኝም ህዝቡን በግዳጅ ከአፉ ላይ ነጥቆ እንዲያዋጣ የተደረገውም በዚሁ ዓመት ነው፡፡

ወያኔ አገራዊ ራዕይ የሌለው .....የሀገርን እና የህዝብን ጥቅም ለባዕድ አሳልፎ የሰጠ..... ለህዝብና ለህሊና ተጠያቂ ያልሆነ...... እቅድን ከፕሮፓጋንዳ ለይቶ የማያውቅ...... በባዶ ሜዳ በቁጥሮች ላይ ብቻ የሚጨፍር ......የህዝቡን አንጀት ያሳረረ እና ያበገነ...... ተስፋ አስቆራጭ ቡድን በመሆኑ ሀገራዊ አጀንዳ ላይ እምነት አይጣልበትም ተብሎ ሲተች የነበረውም በዚሁ ዓመት ነበር፡፡

የአምስት ዓመት የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በሚል በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የባቡር መስመር ለመዘርጋት ከ7 ቢሊዮን ብር በላይ ሊያወጣ እቅድ መያዙ.....የሀገር አቋዋራጭ የባቡር

መስመር ለመዘርጋት ከ100 ቢሊዮን ብር በላይ እንደሚያስፈልገው እያወቀ...... የአስፓልት መንገድ ግንባታ ፕሮግራሞችን መያዙ እየተገለፀ ..... የግልገል ግቤ ቁጥር 3 እና ግልገል ግቤ ቁጥር 4 የመብራት ኃይል ማመንጫ ከ68 ቢሊዮን ብር በላይ እንደሚያስፈልገው እየታወቀ እና አንዱንም ተግባር ላይ ባላዋለበት በዚህ ግዜ የአባይን ግድብ ለመስራት ያልታሰበ እና ዱብ እዳ መፍጠሩ የፖለቲካ ውጥረቱን ለማርገብና መለስ ዜናዊ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ብቻ ተብሎ የተሰራ ስሌት መሆኑ ተረጋግጦዋል፡፡

****

የወያኔው ዋና አቀንቃኝ የነበረውና ከስልጣኑ የተባረረው ኮማንደር ደምሳሽ ኃይሉ የፌዴራል ፖሊስ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የነበረው ግለሰብ ድንገት ከሀገር ወጥቶ መኮብለሉ የተነገረው በዚሁ ዓመት ነው፡፡

አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ ከተሞች ውስጥ የተፈጸሙ ምስጢራዊ ግድያዎችን እና እስከ አሁን ድረስ ብዙ ዜጎች የደረሱበት ያልታወቀ መሆኑን እንደሚያውቅ የሚገመተው ኮማንደር ደምሳሽ ስርዓቱን ጥሎ በእንግሊዝ ሀገር ጥገኝነት መጠየቁም ተረጋገጦዋል፡፡

የወያኔ ቀንደኛ ካድሬ የሆነው ለገሰ አለሙ የተባለው ግለሰብ ለስራ ተብሎ ወደ አሜሪካ ተልኮ የሄደ ቢሆንም በዚያው ስርዓቱን ከድቶ መቅረቱም የተገለፀው በዚሁ ዓመት መገባደጃ ላይ ነው፡፡

በፍትህ ሚኒስትር በምክትል ሚኒስትር ማዕረግ የህግ ጥናት ማርቀቅ እና ማስረጽ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆነው ለገሰ ዓለሙ የተባለው ግለሰብ ከፍትህ ሚኒስትሩ ብርሀን ኃይሉ ጋር ከአሜሪካ ከፍተኛ የህግ ኤክስፐርቶች ጋር ተገናኝተው ለቀናት ውይይት ሲያደርጉ ከሰነበቱ በሁዋላ ስርዓቱን ከድቶ በዚያው አሜሪካ ጥገኝነት ጠይቆ ቀርቶዋል፡፡

በኦሮሚያና በአማራ ክልል የተለያዩ ዞኖች ውስጥ ሲሰሩ የነበሩ ዳኞች በሚደርስባቸው ወከባና እንግልት ብሎም ማስፈራሪያ የተነሳ ስራቸውን በገዛ ፍቃዳቸው እየለቀቁ ወደ መሀል ሀገር ከመምጣታቸውም በተጨማሪ አንዳንዶቹ ቤተሰቦቻቸውን ጥለው ከሀገር እየኮበለሉ መሆኑም የተዘገበው በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ውስጥ ነው፡፡

****

የወያኔ ቡድን የሀገሪቱ ህዝብ በችግር እና በርሀብ እየታመሰ ምሁራኖች በፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ ሀገር እና ህዝብን እንዳያገለግሉ እየተባረሩ ወደ ውጭ ሀገር ሲሰደዱ በአንጻሩ ደግሞ ባዕዳኖች በውጭ ምንዛሪ እየተቀጠሩ የሚመጡበት ዓመት ከመቼውም ግዜ በላይ የዘንድሮው ነበር፡፡

በተለያዩ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በመምህርነት እያገለገሉ ያሉትን ምሁራኖች የደመወዝ እድገት ሳይሰጣቸው ባሉበት እንዲረግጡ እያደረገ በሌላ በኩል ደግሞ ሀገሪቱ መክፈል ከምትችለው አቅም በላይ በውጭ ሀገር ምንዛሬ ከተለያዩ ሀገራት እውቀታቸው አጥጋቢ ያልሆኑትን መምህራኖችን እያስመጣ የሰገሰገበት ዓመትም ይሄው ያሳለፍነው ዓመት ነበር።

ከአዲስ አበባ የኒቨርስቲ ነባር መምህራኖች እና ዲኖች ጭምር እንዲሁም የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንትን አባርሮ በምትካቸው በውጭ ምንዛሪ ከውጭ ሀገር ዜጎችን እያስመጣ መቅጠሩም የዚህ ዓመት አንዱ ክስተት ነበር።

ለአንድ የውጭ ሀገር ዜጋ የዩኒቨርስቲ መምህር በወር ከ30 እስከ 40 ሺህ ብር እየተከፈለው ለኢትዮጵያውያን መምህራኖች ግን ከ3 እስከ 5 ሺህ ብር ብቻ እንደሚሰጣቸውና ይሄም በዝቶባቸው በፖለቲካ አመለካከታቸው እየተንገላቱ ወደ ውጭ ሀገር ሳይወዱ በግድ እየተሰደዱ ያሳለፉበት ዓመት ነበር።

በመላ ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ምሁራኖችን ወያኔ የተለያዩ ሰበቦች እየለጠፈባቸው ወደ እስር ቤት እያጎራቸው ከመሆኑም በላይ በምስጢር በደህንነት ሰዎች እያፈነ የት እንዳሉ የማይታወቁ በርካታ ከመሆናቸውም በተጨማሪ የወያኔን አረመኔ ድርጊት በመፍራት እጅግ ቁጥራቸው የበዙት ሀገራቸውንና ህዝባቸውን ጥለው እየተሰደዱ የሰው ሀገር አገልጋይ ሆነው እንደሚገኙ ይታወቃል።

****

መለስ ዜናዊ የገዛ ካድሬዎቹን በመጠራጠር የግዳጅ እረፍት እንዲያደርጉና በቅርብ ርቀት ላይ በደህንነት እንዲጠበቁ አልፎ ተርፎ የቁም እስረኛ እንዲሆኑና ይህም አልበቃ ሲል ከስልጣናቸው ሲባረሩ የከረሙበት ዓመት ነበር።

በሰሩት ስራ ያልተደሰተው መለስ ዜናዊ የደቡብ ክልል ፕሬዝዳንት ሽፈራው ሽጉጤንና የኦህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣኑን የኢህአዴግ ማዕከላዊ ምክር ቤት አባሉን ዘላለምን ከስልጣናቸው አንስቶ ለወራት በቁም እስረኛነት ሲያዛውዛቸው ከርሞ በቅርቡ ወደ ነበሩበት መልሶዋቸዋል።

ሌላው የጅንአድ ስራ አስኪያጅ የነበረውና የወያኔ አባሉ አቶ ይማም መሐመድ የተባለው ባለስልጣንም የመለስን ጡንቻ የቀመሰው በዚሁ ዓመት ውስጥ ነው።

የወያኔ ተለጣፊ ድርጅቶች በሆኑት በኦህዴድ.... በብአዴን...... በደኢህዴን ባለስልጣናት እና ካድሬዎች መሀከልም ጥብቅ የሆነ ምስጢራዊ ግምገማ ተደርጎ በተለይ ከኦህዴድ እና ከደኢህዴን አዳዲስ እና ነባር ካድሬዎች ከስልጣናቸው እንዲባረሩ ተደርገዋል።

ለመለስ ቅርብ በሆኑት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ የኦሮሚያ ክልል ፌዝዳንት እና የኦህዴዱ ሊቀመንበር አለማየሁ አቶምሳ እና የመለስ አማካሪው ሙክታር ከድር ሰብሳቢነት የተደረገው ይሄው የባለስልጣናት መንጠራ 9 ዋና ዋና የተባሉ የክልሉ የቢሮ ኃላፊዎችን አባርሮዋል፡፡

በመስከረም ወር በተደረገው ሹም ሽረት አዲስ ወጣት ካድሬዎችን ወደ ስልጣን ማመጣት ተብሎ ኃላፊነት የተሰጣቸው እነዚሁ ተባራሪ የወያኔ ባለስልጣናት ነባር ከተባሉት ካድሬዎች ጋር በፍጹም መግባባት ካለመቻላቸውም በላይ የሚያነሱዋቸው ጥያቄዎች ለነመለስ የራስ ምታት ስለሆነባቸው የተባረሩ ሲሆን እነሱም የኦሮሚያ ክልል ባለስልጣናት የፍትህ ቢሮ ኃላፊ ዮሐንስ ምትኩ...የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ ቶሎሳ ደደፉ....ምክትሉ ተስፋዬ አበበ.....የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወንድሙ ቢራቱ.....የመንገድና ትራንስርት ቢሮ ኃላፊ ሁሴን ገልገሉ.....የውሀ ቢሮ ኃላፊ ጀማል አባሶ.....ምክትሉ ግርማ ሰንበታ......የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አሊዩ ዑመር ......የአዲስ አበባ ዙሪያ ዋና አስተዳዳሪ ገላና ኑሬሳ ናቸው፡፡

በተያያዘ ዜና በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የወያኔ ቡድን በአንድ ወገን ላይ ብቻ በጀመረው ምንጠራ የኦሮሚያ ከፍተኛ ባለስልጣንና የኦህዴድ የማዕከላዊ ምክር ቤት አባል የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ የነበረው ዘላለም ጀማነህ ድንገት ሳይታሰብ ከፖሊት ቢሮ አባልነቱ በምስጢር እንዲነሳ ከመደረጉም በላይ ከነበረበት ቦታ ተነስቶ የኦሮሚያ ክልል የግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ ተደርጎዋል፡፡

****

የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ብርሀነ መልካ በበረሀ ስሙ ወዲ ሻምበል የሚባለው የወያኔ ባለስልጣኑን ጨምሮ ሌሎች አራት ባለስልጣናት ድንገት ሳያስቡት እንዲነሱ የተደረገው በዚሁ ዓመት መባቻ ላይ ነበር፡፡

ከእነሱም ተከትሎ በዚሁ መስሪያ ቤት ውስጥ ባሉ ባለስልጣናት መሀከል ሹም ሽረት ተደርጎዋል፡፡ ብዙ እውቀትና ችሎታ ያላቸው መኮንኖች የተንሳፈፉበት ከበረሀ የመጡት ደግሞ መልሰው ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን የተቆጣጠሩበት ዓመት ነበር፡፡

በዚሁ በተደረገው ሹም ሽረት ነባር መኮንን ኮሎኔል አለባቸው የተባለው የሸዋ ሮቢት እስር ቤት ዋና አዛዥ ከስልጣኑ ተነስቶ ቃሊቲ እስር ቤት መምሪያ ተራ ሰራተኛ ሆኖ ሲመደብ ከበረሀ የመጣው ኮሎኔል የማነ የተባለው ደግሞ ከድሬዳዋ እስር ቤት ተነስቶ አዛዥ ወደ ቃሊቲ እስር ቤት የመምሪያ ኃላፊ ሆኖ ተሾሞዋል፡፡ የዝዋይ እስር ቤት ተጠባባቂ አዛዥ የነበረው ከበረሀ የመጣውና የወያኔ ቀንደኛ ባለስልጣኑ ገብረየሱስ የኮሎኔል ማዕረግ ተሰጥቶት መልሶ እዚያው ቦታ ላይ በዋና አዛዥነት የተረከበ ሲሆን የቃሊቲ እስር ቤትን ደግሞ በበላይነት እንዲመራና እንዲቆጣጠር የወያኔው ቁልፍ ሰው ጄኔራል አብርሀም የተባለው መመደቡ ታውቆዋል፡፡

በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ከነዚህ በፊትም 16 የወያኔ ባለስልጣናት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በሚል በጄኔራል ማዕረግ ሹመት የተሰጣቸው ሲሆን እነዚህ አዲስ ተሹዋሚዎችም ሙሉ ለሙሉ የወያኔ ሰዎች መሆናቸውን እና በየመምሪያው ሁለት ሁለት ሆነው እንዲቆጣጠሩ መመደባቸው የሚታወስ ነው::

በዚሁ በተደረገው ሹም ሽረት እና ትርምስ ነባርና በቢሮ ውስጥ ሲያገለግሉ የነበሩ መኮንኖች ከየቢሮው እየተነሱ ወደ ጥበቃ እየተመደቡ ሲሆን ብዙዎቹ ደግሞ ወደ ስራ ሳይመደቡ ተንሳፍፈው ቀርተዋል::ይህንኑ ትርምስ ተከትሎ ቁጥራቸው ከ100 በላይ የሆኑ የመስሪያ ቤቱ ፖሊሶች መልቀቂያ ያስገቡትና የለቀቁትም በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ነበር::

****

ለአንድ ዓመት ያህል ሲታሽ እና ሲድበሰበስ የነበረው አዲሱ የታክሲ ስምሪት ስራ ላይ በዋለ ጥቂት ቀናት ውስጥ ምደባው በቂ ጥናት ያልተደረገበት በመሆኑ ስራው አያዋጣንም በማለት የታክሲ ሹፌሮች የስራ ማቆም አድማ ባለፈው አመት መትተው ነበር::

አዲሱ የስምሪት መስመር የህዝብ ብዛትንና የመኪና አቅርቦትን ያላገናዘበ በይድረስ ይድረስ ብቻ የተዘረጋ ነው በማለት አድማ በመምታታቸው አዲስ አበባን ጭር አድርገው ህዝቡም ለቀናት ከቤቱ ሳይወጣ የነበረው በዚሁ ዓመት ነበር::

የታክሲ ባለንብረቶች ፤ ሹፌሮችና ረዳቶች ያቀረቡት ጥያቄ ምላሽ በማጣቱ በአዲስ አበባ ታክሲዎች የተጀመረውን የስራ ማቆም አድማ በማጠናከራቸው ከተማዋ ጭር ብላ ህዝቡም በትራንስፖርት እጥረት ተቸግሮ ነበር ::

የታክሲ ስራ ማቆም አድማን ተከትሎ ፖሊሶችና የታክሲ አሽከርካሪዎች ግጭት ፈጥረው በቡጢ ሲቡዋቀሱ የተስተዋለ ሲሆን ህዝቡም በቁጣ በመነሳሳት በፖሊሶች ላይ አደጋ ሲያደርሱ የነበረውም በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ነው::

በአዲስ አበባ በተለያዩ ቦታዎች ሹፌሮችና ፖሊሶች ግጭት ፈጥረው ፖሊሶች በመሳሪያና በጀርመን ሰራሽ ዱላ .......ሹፌሮችና ረዳቶች ሆነው ደግሞ በድንጋይ ሲፋለሙ የነበረ ሲሆን በተለይ ብርጭቆ ፋብሪካ ተብሎ በሚጠራው ሰፈር ውስጥ በሚገኘው የኮንዶሚኒየም ግቢ ውስጥ ከፍተኛ ድብድብ ተከስቶ ብዙ ፖሊሶች ተፈንክተው ከአካባቢው የተባረሩ መሆኑን በወቅቱ መዘገባችን የሚታወስ ነው::

በታክሲዎች የተጀመረው የስራ ማቆም አድማ ወደ ሌሎች ይዛመታል የሚል ፍርሀት የገባው የወያኔ ቡድን በደህንነት ሰራተኞች እና በፖሊስ በኩል ውስጥ ውስጡን የአድማው ቀስቃሽ ናችሁ በሚል ሹፌሮችን ከየቤታቸው እየለቀሙ ኮልፌ በሚገኘው የተወርዋሪ ፖሊስ ካምፕ ውስጥ በማስገባት

ይህ ቀረሽ የማይባል የዱላ ድብደባ የፈጸሙባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ለአራት ቀናት ጠዋት ጠዋት የቀዘቀዘ ውሀ በተሞላ በርሜል ውስጥ እራቁታቸውን ለአንድ ሰዓት ያህል እንዲቆዩ ተደርገው ነበር፡፡

በተመሳሳይ ዜና አንበሳ የከተማ አውቶቡስ ሰራተኞች እና የቲክኒክ ሰራተኞች በወያኔ ካድሬዎች የሚደርስባቸውን አስተዳደራዊ በደል በመቃወም ለሁለት ቀናት የስራ ማቆም አድማ አድርገዋል፡፡

ከአንድ ሺ በላይ ሹፌሮች እና መካኒኮች በአድማው ላይ የተሳተፉ ሲሆን የአድማው ዋና አላማ ወያኔ የሾማቸው የድርጅቱ አመራሮች በሹፌሮቹ እና በሰራተኞች ላይ ጥብቅ ደንብ በማውጣታቸው የተነሳ መሆኑም በወቅቱ ተዘግቦዋል፡፡

ከ30 ዓመት በላይ ስናሽከረክር የረባ የደመወዝ ጭማሪ ሳታደርጉና የተሻለ ምቹ ሁኔታ ሳትፈጥሩ በእኛ ላይ አስተዳደራዊ በደል እየፈጸማችሁብን ስለሆነ የአዲስ አበባ ህዝብ ብሶታችንን እንዲሰማን ስራ ማቆም አድማ አድርገናል በማለት የያዙትን አውቶቡሶች በያሉበት ገትረው ለሁለት ቀናት የስራ ማቆም አድማ ያደረጉ ሲሆን እነሱን ተከትሎ መካኒኮችም የስራ ማቆም አድማ አድርገው እንደነበር አይዘነጋም፡፡

****

እንደ ሌሎች የሀገሪቱ ህዝቦች ሁሉ የትግራይ ተወላጆችም በመቀሌ ከተማ ዙሪያ የሚገኙ የእንደርታ ቀበሌ ነዋሪዎች በወያኔ ፈጥኖ ደራሽ እና የፌዴራል ፖሊሶች ድብደባና ወከባ የደረሰባቸውም በዚሁ ባገባደድነው ዓመት ውስጥ ነው፡፡

በማዘጋጃ ቤት በኩል ህጋዊ በሆነ መንገድ ቦታ የተሰጣቸውና ቦታው ላይ ቤት ሰርተው መኖር ከጀመሩ ከ10 ዓመታት በላይ ያስቆጠሩ የመቀሌ ነዋሪዎች ቤታቸው ድንገት እንዲፈርስ በከተማዋ ካድሬዎች ውሳኔ በመሰጠቱ አቤቱታ ለማቅረብ በተዘጋጁት ዜጎች ላይ ቅልብ የክልሉ ፈጥኖ ደራሽ ፖሊሶች እና በፌዴራል ፖሊስ ከፍተኛ ድብደባ ከመፈጸሙም በላይ ቁጥራቸው የበዙ ነዋሪዎች ተፍሰው ለእስር የተዳረጉትም በዚሁ ግፍና መከራ በተፈጸመበት ዓመት ነበር፡፡

የደረሰባቸውን ግፍ እና በደል ለመግለፅ ሰላማዊ ሰልፍ እንዳያደርጉ የተከለከሉት እነዚሁ አቤቱታ አቅራቢ የመቀሌ ነዋሪዎች አቤቱታ ለማቅረብ ቀርቶ በህብረት አንድ ላይ ቆመው በመነጋገር ላይ እንዳሉ ከየት መጡ ሳይባል የፌዴራል ፖሊሶች በአስለቃሽ ጭስ እየተጠቀሙ ከየሰፈሩ እያባረሩዋቸው ከመሆኑም በላይ ሴት ወንድ...... አሮጊት ሽማግሌ...... እርጉዝ እመጫት...... ሳይሉ ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል፡፡

የሚያሳዝነው እና የሚያሳፍረው የወያኔ ባለስልጣናት የሚታረስ መሬት አይሸጥም አይለወጥም በማለት ከኖርንበት ቤታችን በፖሊስ እየበደቡ ቢያስወጡንም ዛሬ በመላ ሀገሪቱ ውስጥ በሺህዎች የሚቆጠሩ የገበሬ ማሳዎችን እየነጠቁ ለውጭ ሀገር ዜጎች እያከፋፈሉ ያውም የሀገር ሀብት የሆነውን ደን እያስጨፈጨፉ እያየንና እየሰማን ለእኛ እንዲህ ያለ ምላሽ መስጠታቸው እውን እኛ

ማን ነን ብለን እራሳችንን ለመጠየቅ ከመገደዳችንም በተጨማሪ መላው የሀገሪቱ ህዝቦች ምስጢሩን አውቆ የበኩሉን ሊወጣ ይገባዋል ሲሉም ጥሪ ያቀረቡት በዚሁ ወቅት ነበር፡፡

ሌላው አስገራሚ ነገር በተፈናቀሉበት ቀበሌ ውስጥ አርሴማ ማርያም የተሰኘች ቤተክርስቲያን የምትገኝ በመሆኑ እሱም ይፈርሳል በመባሉ የተደናገጡት የአካባቢው ህዝብ ታቦቱን ተሸክሞ ባለስልጣቱን ለመማጸን በአደባባይ ላይ ቢወጣም ታቦት የተሸከሙትን የእምነት አባቶች ጭምር በአልሞ ተኩዋሽ እና ቅልብ የወያኔ ታጣቂ ኃይሎች ጭምር በቆመጥ ቀጥቅጠው ለበሽታ የዳረጉዋቸው በዚሁ ባለፈው ዓመት ነበር፡፡

****

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጳጳሳት መሀከል እንደ ሌሎቹ ዓመታት ግዜ ሁሉ ያሳለፍነው ዓመትም በንትርክ እና እርስ በርስ ሽኩቻ ተንሰራፍቶ ምዕመናን ግራ ተጋብቶ የነበረበት ወቅት ነበር፡፡

በዓመት ሁለት ግዜ የሚሰበሰበው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ የዘንድሮው የመጀመሪያ ስብሰባ ጥቅምት ላይ ተደርጎ የአባ ጳውሎስ ምስሎች ከየአደባባዩና ከየቤተክርስቲያኑ እንዲወርድ ሐውልታቸውም እንዲፈርስ ብሎ የወሰነውም በያዝነው ዓመት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የሲኖዶሱ ውሳኔ የወረቀት ላይ ነበር ብቻ ሆኖ ሀውልቱም ሳይፈርስ በየቤተክርስቲያኑም የተሰቀለው ምስላቸው ሳይነካ ነው ዓመቱ የተጠናቀቀው፡፡

በዚህም ምክንያት የተነሳ በአባ ጳውሎስ እና በጳጳሳት መሀከል ሲኖዶሱ ያሳለፈው ውሳኔ ሳይፈጸም በመቅረቱ ሰጨቃጨቁና ሲነታረኩ ያሳለፉበት ዓመት ነበር፡፡

በተለይ የአባ ጳውሎስ ቀኝ እጅ ሆና ጳጳሳቱን እና በየቤክስርቲያኑ ያሉትን አለቆች እያስፈራራች እንደልብዋ የምትፈነጨው የእጅጋየሁ በየነ ጉዳይም በዚሁ በያዝነው ዓመት የሲኖዶሱ ዋነኛ አጀንዳ ሆኖ የተነሳ ከመሆኑም በተጨማሪ ጳጳሳቱ በቁጣ ከማውገዛቸውም በላይ ዳግመኛ ወደ ቤተክህነት ግቢ እንዳትገባ የተወሰነባትም በዚሁ ዓመት ነበር፡፡

በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ውስጥ ከአባ ጳውሎስ ጋር የማይግባቡ ድርጊታቸውን በጽኑ የሚኮንኑ እና የሚተቹ የነበሩት አባት ድንገት በምግብ መመረዝ ተብሎ የሞቱት አቡነ መልከ ፀዲቅ የጳጳሳት እና የአባ ጳውሎስ ንትርክ እና ጭቅጭቅ በጠነከረበት ሰሞን ነበር፡፡

****

የወያኔ ቡድን በህዝቦች ላይ የሚፈጥረውን ጫና እና የሚሰጣቸው የትምህርት ጥራት ዝቅተኛ ነትንና እንዲሁም የሚደርስባቸውን የተለያዩ  በደሎች በመቃወማቸው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እየተመነጠሩ ለእስር የተዳረጉት በዚሁ ዓመት አጋማሽ ላይ ነበር።

በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ወያኔ ተማሪዎቹን ከየመኝታ ክፍላቸው በምሽት ድንገት ሳያስቡት እየለቀመ ለእስር እየዳረጋቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ወደየት እንደሚወስዳቸው ባለመታወቁ ቤተሰቦቻቸው ለከፍተኛ ጭንቀት ተዳርገው ሲሰቃዩ የነበረበት ዓመት ነው።

ወያኔ ለአገዛዙ እንዲያመቸው በተማሪዎቹ  መሀከል እርስ በርስ ብጥብጥ እንዲቀሰቀስ አድርጎ መልሶ በፌዴራል ፖሊስ እያፈሰ ወደ ተለያዩ የወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፖች ሲያጉራቸውና በድብደባ ሲያሰቃያቸው የከረመውም በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ውስጥ ነው።

በተለይ በአዲስ አበባ፣ በአዳማ፣ በቲፒ ፣በዲላ፣በአርባ ምንጭ፣ በአለማያ፣ በባህርዳር፣ በጅማ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ በተከሰተ ብጥብጥ ከአስር ተማሪዎች በላይ የተገደሉ ከመሆኑም በተጨማሪ ብዙ ተማሪዎች ተጎድተው የነበረበትና ሆስፒታል ለወራት ያህል ተኝተው የከረሙ ሲሆን ቁጥራቸው የበዛ ተማሪዎችም በእስር ሲሰቃዩ ከርመዋል።

ከየዩኒቨርስቲው ታፍሰው የሚወሰዱ ተማሪዎች ወዳልታወቀ እስር ቤት እየተወሰዱ ከመደብደባቸውም በላይ ቤተሰቦቻቸው በጭንቀት በፍለጋ ሲባዝኑ የከረሙበትና በዚሁ ጭንቀት ሳቢያ ትምህርታቸውን ያቋረጡ እጅግ ቁጥራቸው በርካታ  ተማሪዎች ናቸው።

****

ገበሬውን ከግብርና እፈናቀለ ለልመና እየዳረገ....... ወጣቱን ትውልድ በማይረባ የትምህርት ፖሊሲው እንዲደናቀፍ እያደረገ አልፎ ተርፎ ትውልድ ገዳይ በሆኑ መርዛማ ሱሶች እንዲጠመዱ እያደረገ ወደ ጎዳና ህይወት እያስወጣ ያለው ወያኔ  ከተማ አቆሸሻችሁ በሚል ዜጎችን ከአዲስ አበባ እያፈሰ ወደ ፍቼ የጦር ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ ያጎራቸውም በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ውስጥ ነው።

በመልሶ ማልማት ስም ለዘመናት ከኖሩበት ቤት እያፈናቀለ ለጎዳና ህይወት የዳረጋቸውን ዜጎች ጨምሮ በተለያዩ ወያኔ ሰራሽ መሰሪ ተግባሮች ወደ አዲስ አበባ ጎዳና ህይወት የወጡትን ዜጎች ርሀብ የእለት ጉርሴ..... ድንጋይ ትራሴ..... ላስቲክ ብርድ ልብሴ .......ኑሮ ብለው እየተሰቃዩ ያሉትን ዜጎች ከተማ ታቆሽሻላችሁ እያለ ከተኙበት ድንገት ሌሊት  በመከላከያ ወታደሮች አፍሶ ወስዶዋቸዋል።

በሌላ ዜና  በነቀምት ...በደምቢዶሎ...በአምቦ....... በባሌ .....በአርሲ እና በናዝሬት ከተሞች ውስጥ ህዝቡ እንደ ሰሜን አፍሪካ የአረብ ሀገራት  አመጽ እንዲያነሳ ሲቀሰቅሱ ነበር በሚል ዜጎች በቀን በጠራራ ፀሀይ.....በሌት በድቅድቅ ጨለማ..... እየታፈሱ ለእስር ሲዳረጉ የነበረውም በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ነው::

በተለይ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በህዝቡ ላይ ከፍተኛ ክትትል እና ቁጥጥር ከመደረጉም በላይ የአመፅ ሊያቀጣጥሉ ይችላሉ  እየተባሉ ወዳልታወቀ ስፍራ እየታሰሩ ሲሆን ከምዕራብ ኢትዮጵያ ወደ ደቡብ ጠረፍ ቦረና የቦረናውን ወደ ደምቢዶሎ እያቀያየሩ ስያሰቃዩዋቸው ከመክረማቸውም በተጨማሪ በተለይ ዋና ናቸው የተባሉትን ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ያፈሱዋቸውን በማዕከላዊ እስር ቤት እንዳጎሩዋቸውና የውስጥ እግራቸውን ሲገረፉ እንደከረሙም የተጋለጠው በዚሁ ዓመት ነበር::

የወያኔ የግፍ አገዛዝ የሰለቸውና የተማረረው ህዝብ አንዴ በፖለቲካ አመለካከቱ ሌላ ግዜ በኑሮ ውድነት ባሰማው ብሶት በደህንነት እና በፌዴራል ፖሊስ እየተንገላታ እና እየተሰቃየ በገዛ ሀገሩ እንደ ባዕድ ተቆጥሮ ሲታሰር ሲፈታ ለ20 ዓመታት የቆየ ቢሆንም ዘንድሮ ግን የግፉ መጠን ጨምሮ ከመግደል እስከ ማሰደድ..... ከመደብደብ እስከ አካለ ስንኩልነት የተዳረገበት ዓመት ነበር::

****

የወያኔ ቡድን ለማስመሰል እና ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲል ብቻ ያለ በቂ ጥናት እና ውይይት በነሲብ የዋጋ ተመን አወጣሁ ቢልም በከተማዋ በተለይ በአፍሪካ አንደኛ ነው በሚባለው በመርካቶ የንግድ ማዕከል ውስጥ  የእቃ እጥረት ተፈጥሮ ህዝቡ ለከፋ ችግር የተዳረገበት ዓመት ነበር::

ነጋዴውን እና ተጠቃሚውን ህዝብ ሳያማክርና ሳያወያይ የወያኔ ቡድን ድንገሀት ለፖለቲካ ፍጆታው ብቻ ሲል ባወጣው የዋጋ ተመን በመበሳጨት ነጋዴዎች እቃ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት በማቆማቸው ለወራት ህዝቡ ለከፋ ችግር ተዳርጊ ነበር ያሳለፈው::በዚህም የተነሳ መርካቶ የገበያ ማዕከል በህዝብ ብዛት እና እቃ ፈላጊዎች ብዛት ስትተራመስ ነበር የከረመችው::

****

ለህወሀት ታማኝ አገልጋይና ሎሌ በመሆን በህዝቡ ላይ ከፍተኛ በደል ሲፈፅም የነበረው የቀድሞው ኢህዴን የአሁኑ ብአዴን 30ኛ ዓመት በዓሌን አከበርኩ በማለት ለአንድ ወር ያልተቋዋረጠ ግብዣ በማድረግ በመላ ሀገሪቱ ላሉ  ካድሬዎቹ ሲያንበሸብሻቸው የከረመው በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ነው::

እወክለዋለሁ የሚለው የአማራ ህዝብ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በርሀብ እና በችግር እግር ከወርች ተጠፍረው ባሉበት  ወቅት የህወሀት ተቀፅላ የሆነው  ብአዴን ይባስ ብሎ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ከአርሶ አደሩ፤ከነጋዴውና ከህዝቡ ላይ  በግዴታ በሰበሰበው ገንዘብ በተለያዩ ከተሞች

ውስጥ ተበትነው ያሉትን ካድሬዎች በግብዣ ያንበሸበሸ ከመሆኑም በላይ በባህርዳር ከተማ ሌሊቱን ዳንኪራ ሲደለቅና ሲመታ  ያነጉ ሲሆን ከቻይና  በውድ ዋጋ በተገዙ ርችቶች ከተማዋንና ህዝቡን ሲያምሱት ነው ያደሩት፡፡

በበዓሉ ዋዜማ ላይም የብአዴን ካድሬዎች በተለይ ቀድሞ የኢህዴን ነባር ታጋይ ናቸው የተባሉትን በባህር ዳር ከተማ በምስጢር ሰብስበው የመደለያ የእራት ግብዣ ያደረጉላቸው ቢሆንም በወቅቱ እጅግ አነጋጋሪ ጉዳዮችን አንስተው ሲከራከሩ እንደነበርና ለግዜው ነገሩን ትተን 30ኛ ዓመት በዓላችንን በደመቀ ሁኔታ እናክብር ......የበዓሉን መንፈስ አትበጥብጡ በማለት አዲሱ ለገሰ ፣በረከት ስምኦን እና የወቅቱ ሊቀመንበር ደመቀ መኮንን ነባር ካድሬዎቹን ሲያስፈራሩ የነበረውም በዚሁ አከበርን ባሉት በዓል ላይ ነበር፡፡

በተለይ በዚሁ ምሽት ላይ የተነሳው የነባር ካድሬዎቹ አከራካሪ ጉዳይ ከበረሀ ጀምረን አብረን ደምተን እና አጥንታችንን ከስክሰን ስልጣን ለ20 ዓመታት እንደ እርስት በአንድ ቡድን ብቻ መያዙ ተገቢ አለመሆኑን አንስተን በቅርቡ መፍትሔ ያገኛል ብላችሁ ነበር ......አሁን ግን እንደምናየው ፍፅሞ መሻሻል ያልታየበት የበለጠ የአንድ ግለሰብ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ የሰፈነበት የሆነበት ምክንያት ምንድነው? ያነሱት ዋነኛ ጥያቄ አንዱ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ የመለስ ተላላኪና ጉዳይ አስፈጻሚ  በሆኑት አዲሱ ለገሰ፣በረከት ስምኦን እና ደመቀ መኮንን በኩል በተለመደ ሾኬያቸው ተጠቅመው የካድሬዎቹን ጥያቄ አድበስብሰው አስቀርተውታል፡፡

****

ዘንድሮ ለወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ትልቅ እራስ ምታት ሆኖ ከነበረው መሀከል አንዱ የኦህዴድ ካድሬዎች ማመጽ ነበር፡፡

ለ20 ዓመት  ስልጣን እርስቱ ያደረገው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ለቀጣይ አምስት አመት በድጋሚ ተደረገ በተባለ ምርጫ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ የያዘ ቢሆንም በወቅቱ የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባሎች በመቃወም ከፍተኛ ብጥብጥ አንስተው መለስን ክፉኛ ሲተቹና ሲቃውሙ የተደመጠውም በዚሁ ዓመት ነበር፡፡ይሁን እንጂ የኦህዴድ ባለስልጣናት በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ያደረጉት ተቃውሞ ባለመኖሩ መለስ ዜናዊ  ዋነኛ ቀንደኛ እና አስተባባሪ ናቸው ያላቸውን ከነበሩበት ቦታ እያነሳ በቅርብ ርቀት የሚቆጣጠርበት ቦታ እየወሸቀ ያስቀመጣቸውም በዚሁ ወቅት ነበር፡፡

በዚህም የተነሳ የኦህዴድ አመራር ላይ ምንጠራ አድርጎ እስከ ቀበሌ ድረስ ከመውረዱም በላይ በአባዱላ ግዜ የነበሩ ሁሉም አመራሮች ቀስ በቀስ እየተነሱ በአዳዲስ እየተተኩ ከመሆኑም በተጨማሪ አባዱላም ከኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንትነት ተነስቶ አለማየሁ አቶምሳ የተሰኘ ግለሰብ በቦታው እንዲተካ አድርጎዋል፡፡

በኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቲ አባሎች በኩል የተነሳው ዋነኛ ተቃውሞ የነበረው መሪዎች በየአምስት አመቱ መለወጥ አለባቸው...... አባል ድርጅቶች የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ መያዝ አለባቸው..... በአንድ ግለሰብ ብቻ ለ20 ዓመት ስልጣን መያዝ የለበትም በማለት አዳማ ላይ ተደርጎ በነበረው ጠቅላላ ጉበኤ ጥያቄና ተቃውሞ ተነስቶ እንደነበርና ይህንኑ ለማርገብ ሲባል የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቲን ለብቻ ሰብስበው በፌዴራል ፖሊስ አስከብበው በማስፈራራት በግዴታ የመለስን መሾም እንዲቀበሉ የተደረገውም በዚሁ ወቅት ነው።

በተለይ ኦህዴድ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ የማይረከብ ከሆነ አባዱላ ገመዳ ከኦሮሚያ ክልል ፊዝዳንትነት አይነሳም በማለት የክልሉ ምክር ቤት እና ማዕከላዊ ምክር አባሎች በሙሉ ድምፅ ወስነው የነበረ ቢሆንም ኩማ ደመቅሳ ...ሙክታር ከድር በተሰኙ የመለስ ደጋፊዎች የተነሳው ጥያቄ ሁሉ ውድቅ ሆኖ መለስ በፈለገው መንገድ ተጉዞ ኦህዴድ አመራሮች እንዲበታተኑ ተደርጎዋል።

በቡራዩ አቅራቢያ በሚገኝ እስር ቤት ከታሰሩት 120 በላይ የኦህዴድ ከፍተኛ በለስልጣናት መሀከል ከጥቂቶቹ በስተቀር አብዛኛዎቹ የካቢኔ አባሎች ሲሆኑ ሌሎችም ከፍተኛ ባለስልጣናት ከቦታቸው እየተነሱ ወደ ዝቅተኛ ቦታ እንዲቀመጡ የተደረገውም በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ውስጥ ነበር።

መለስ የክልል ፕሬዝዳንቶችን ለመቆጣጠር እንዲያመቻው አዲስ አደረጃጀት በመቅረጽ ኦሮሚያ አራት ፤አማራ ሶስት፤ ትግራይ ሁለት ፤ደቡብ አራት ምክትል ፕሬዝዳንቶች እንዲሾሙ ተደርገዋል።

****

በሀገሪቱ ርሀብ ነግሶ......ኑሮ ውድነቱ ተባብሶ...... ዜጎች በችግር እየተገረፉ ባለበት ወቅት የወያኔ ቡድን 50 ሜትር ያለው ኬክ አስጋግሮ ያበላበት ዘመን ነበር ዘንድሮ። አጼ ኃይለ ስላሴ ለልደት በዓላቸው ከእንግሊዝ አስጋግረው አስመጡ እያለ ህዝቡን ሲቀሰቅስባቸው እንዳልነበር ዘንድሮ እሱ ብሶ 50 ሜትር ርዝመት ኬክ አስጋግሮ በፌሽታ አሳልፎ ነው የከረመው የወያኔ አረመኔ ቡድን።

ህዝቦች በኑሮ ውድነት እና በችጋር እየተቆሉ እና ወያኔ በፈጠራቸው ምክንያቶች አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ባሉበት በአሁኑ ግዜ የወያኔ ባለስልጣናት በኬክ እና በጮማ እየተምነሸነሹ ከመሆኑም በተጨማሪ ለቅንጦት 50 ሜትር ርዝመት ያለው ኬክ መቁረሱ በመላ ሀገሪቱ ህዝቦች ዘንድ በሀዘን ያሳለፈበት ጊዜ ነበር።

የሚያሳዝነው እና የሚያሳፍረው ከድሀ ቤተሰብ ተወልዶ እና በጥረቱ አንቱ የተሰኘው የዓለማችን ኮከብ አትሌት ኃይሌ ገብረ ስላሴ ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር በመሆን በቦታው ላይ የክብር እንግዳ ሆኖ ከመገኘቱም በተጨማሪ ኬኩን መቁረሱ ሳያንሰው የተራበውን ህዝብ ረስቶና ዘንግቶ ወያኔ በቀደደለት ቦይ መፍሰሱ እና የወያኔ አረመኔ ቡድን አድማቂ ሆኖ መገኘቱ ህዝቡን ያበሳጨውም በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ነበር።

****

በጅማ ከተማ አቅራቢያ በሚገኘው አሰንዳቦ በተባለች አነስተኛ ከተማ በተቀሰቀሰ የጥፋት ዘመቻ አንድ ሰው ሲገደል በሺህዎች የሚቆጠሩት ቤት ንብረታቸውን ጥለው ተሰድደዋል።

ወያኔ በሚደርስበት ውስጣዊና ውጫዊ ጫና ምክንያት የራሱን ልጣን ለማደላደልና የአገዛዝ እድሜውን ለማራዘም ሲል በብሔር እና በሀይማኖት እየከፋፈለ ለማጋጨት ባወጣው እቅድ መሰረት ተግባራዊ ያደረገው ይሄው የጥፋት ተልዕኮ ባሳለፍነው ዓመት በጅማ አቅራቢያ በሚገኙ መንደሮች በተፈጠረ ውዝግብ ከ55 በላይ ቤተክርስቲያኖች እና ቤቶች ጋይተዋል።

ወያኔ ባደራጃቸው እራሳቸውን አክራሪ የሙስሊም እምነት ተከታዮች ነን በሚሉ ቡድኖች የተጀመረው የጥፋት ተልዕኮ ለተከታታይ ሶስት ቀናት የተካሄደ ሲሆን በነዚሁ ቀናት ውስጥ አንድ የክርስትና እምነት ተከታይ በተኛበት ከነቤቱ የተቃጠለ ሲሆን ሌሎች 20 መኖሪያ ቤቶችም ሙሉ ለሙሉ ወድመዋል።

ለዘመናት ታፋቅሮና ተከባብሮ በኖረው ህዝብ መሀል እልቂት እና ጥፋት እንዲፈፀም መርዘኛ ፕሮፓጋንዳ እየነዛ ከመሆኑም በተጨማሪ በቡድን እያደራጀ ሙስሊሙን ከክርስቲያኑ እያጋጨ የነበረውም ባሳለፍነው ዓመት ውስጥ ነው።

ማንነታቸው እንዳይታወቁ እና እንዳይታዩ ፊታቸውን ጠምጥመው የመጡት እነዚሁ የወያኔን ተልዕኮ ፈጻሚ ኃይሎች በተሰማሩበት የጥፋት ቦታዎች ሁሉ ያገኙትን ቤት እና ንብረት እየለኮሱ ከማጋየታቸውም በላይ አዛውንቶችን እና አሮጊቶችን በዱላና በአለንጋ እንደ ህፃን እየገረፉ ሲያሰቃዩዋቸው እንደነበረም ተዘግቦዋል።

ኦሮሞውን ከሱማሌው...አፋሩን ከአማራው...ከንባታውን ከወላይታው...አኙዋኩን ከኑዌሩ...ራያውን ከአክሱሙ .....እያላተሙና እያጋጩ የበሰበሰና የተደረተ ስልጣናቸውን ለመቀጠል እየጣሩ ባለት ወቅት ይባስ ብለው በጅማ ዙሪያ በሚገኙ ከተሞች 55 ቤተክርስቲያናትን እንዲቃጠል አድርገው ሙስሊሞች ያደረጉት አስመስለው ክርስቲያኑን ከእስላሙ ለማጋጨት ሙከራ ያደረጉትም በዚሁ ዓመት ነበር።

****

እስከ ዛሬ ድረስ እልባት ያልተገኘለት ........ መቁዋጫ ያልተሰጠው....... ከ80 ሺህ በላይ የሀገሪቱ ዜጎች ደማቸውን አፍስሰው..... አጥንታቸውን ከስክሰው...... አካለ ጎዶሎ ሆነው የሞቱበትን የባድመ ውጊያ የድንበር ግጭት አይደለም ሲል እብሪተኛው የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ ተናገረው በዓመቱ መገባደጃ ላይ ነበር።

ወያኔና ሻዕቢያ በረሀ እያሉ ኢትዮጵያን ለማፈረስ ሲማማሉ የነበሩት ሁለቱ እብድ መሪዎች በፈጠሩት ግጭት ከ80 ሺህ በላይ ዜጎች የተሰውበትን ትልቅ ገድል አንኩዋስሶና አዋርዶ የድንበር ግጭት ሳይሆን ያለ መግባባት ነው በማለት እንደ ተራ ነገር መግለጫ መስጠቱ በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ብስጭት ቀስቅሶም ነበር።

ታሪክ በራዥ እና ከላሽ የሆነው የወያኔ ቡድን ጀግኖች አባቶቻችን በከፈሉት መስዋዕትነት የተገኘውን የአድዋን ድል ለመንኩዋስስ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ የነበረውም በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት መገባደጃ ላይ ነበር።የመለስ ቀኝ እጅ የሆነው የህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣኑ ስብሀት ነጋ የአድዋ ድል መታሰቢያ የሆነው የአፄ ምኒልክ ሐውልት እንዲፈርስና ወደ አድዋ እንዲሄድ ከመቀስቀሱም በላይ በአፍሪካ ህዝብ ጭምር ኩራት እና የጥቁር ህዝቦች መገለጫ የሆነውን የአድዋ ድል ለመጨፍለቅና ጨርሶ ደብዛው እንዲጠፋ ለማድረግ እየተራወጠ የነ በረውም ያሳለፍነው ዓመት ነው።